# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

## ለሰፊው ሕዝብ

(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር)

መብትና ጥቅም

## የሚታገል ጋዜጣ

ልዩ እትም ታህሣሥ 19 ቀን 1990 ዓ.ም.

### የሰማእታት ድርጅታችን ይፋረዳል እንጂ አይፈረድበትም

ከወጣትነት ዘመኑ አንስቶ መጀመሪያ በስመ ጥሩው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በኋላም ከነሐሴ 1960 ዓ.ም. ጀምሮ የመላ ኢትዮጵያ ሶሽያሊስት ንቅናቄ መሥራች አባል በመሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ክብር፤ ለፍትህና ለብልጽግና ሕይወቱን ሲሰዋ የቆየው ሃቀኛ መርያችን አበራ የማነአብ ታህሣሥ 19 ቀን 1990 ዓ.ም. በወያኔ ፍርድ ቤት ይቀርባል።

ወንድማችን አበራ በዚህ መልክ ለወንጀለኛው ወያኔ ፍርድ ቤት በሚቀርብበት እለት የመላ ኢትዮጵያ ሶሽያሊስት ንቅናቄ አመራር በመላ አባሎቹና ደጋፊዎቹ፤ በድርጅቱ አርማ ስር ተሰልፈው ለዚች አገር ደህንነትና ብልጽግና ሲዋደቁ በተሰው ገበሬዎችና ወዛደሮች፤ ሴቶችና ወጣቶች፤ ምሁራንና ዲሞክራቶች፤ መለዩ ለባሾችና ሌሎች አገር ወዳድ ዜጎች ስም አንድ ነገር ግልጽ እንዲሆን ይፈልጋል። ይህ ታጋይ መሪያችን ለወያኔ ፍርድ በመዳረግ ላይ ያለው በግሉ በፈጸመው ምንም ወንጀል እንዳልሆነ ጠንቅቀን ስለምናውቅ ማንኛውም የሚመሠረትበትን ክስ በድርጅታችን ላይ እንደተመሠረተ ክስ አርገን እንደምንቆጥረው ከወዲሁ ግልጽ መሆን ይኖርበታል።

ይህ በድርጅታችን ላይ የተመሠረተ ክስ ሁለት ገጽታዎች አሉት። በአንድ በኩል የዚህ ክስ እውነተኛው ገጽታ አለ። ይኸውም ከወያኔ ጋር ያለው የፖለቲካ ልዩነት ነው። በሌላ በኩል ደንሞ የሰበቡ ገጽታ አለ። ይህ ደግሞ በአበራና በድርጅታችን ላይ ሲሰነዘር የሚሞከረው የቀይ ሽብር አራማጅነት የተባለው የፈጠራ ክስ ነው።

የፖለቲካ ልዩነትን በተመለከተ ወያኔ ሲያመቸው በፈጠራ ክሶች እየወነጀለ በተቃዋሚ ዜጎችና ድርጅቶች ላይ አስፈረድኩ ማለቱ ሁሉም ዜጋ የሚያውቀው ጸረ ዲሞክራሲያዊ ስለቱ ነው። ይህ አልሳካ ሲል ደግሞ ተቃዋሚዎችን በጠራራ ፀሐይ በጥይት መደብደብ፤ ማሰር፣ ማተቃየት የግፈኛው አገዛዝ የእለት ተእለት ተግባር በመሆኑ በሃገር የመጣ መአት ነውና ተባብረን እንታገለው ከማለት ሌላ የምንጨምረው ነገር የለንም።

ምናልባት ሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎችን ለመዋጋት ከሚጠቀምባቸው ርካሽ ዘዴዎች በድርጅታችን ላይ የተመሠረተው ክስ ለይት የሚልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ይኸውም

ወያኔ ያዋጣ ስለመሰለው ድርጅታችንን ዛሬ በሚያሳየው ተቃውሞ ሳይሆን የዛሬ 20 ዓመት ይዞት በነበረው የፖለቲካ አቋም በተከተለው የትግል ስልት እፋረዳለሁ ባይ መሆኑ ነው።

የዛሬ 30 ዓመት አበራ የማነአብና ሌሎች ሰማዕት መሪዎቻችን ለጋ ሕይወታቸውን ለዚች ሃገር ክብር፤ አንድነት፣ ደህንነትና ብልጽግና ለመሰዋት ተማምለው ሲነሱና የመላ ኢትዮጵያ ሶሽያሊስት ንቅናቄን ሲመሰርቱ የዚህ ወይም የዚያ ብሄር ሳየሆን የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሙሉ ለብሄራዊ ነጻነትና ለአንድነት ያላቸውን የጋራ ህልም፤ የዚህ ወይም የዚያ ብሄር ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ለእኩልነትና ለወንድማማችነት ያላቸውን የጋራ ራዕይ፤ የዚህ ወይም የዚያ ብሄር ሳይባል የመላ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ለማህበራዊ ፍትህ ያላቸውን የጋራ ጥማት፤ ለዲሞክራሲና ለሰላም ያላቸውን የጋራ ጉጉት ለሚያንጸባርቅ አቋም አንግበው ተነስተዋል።

ይህንን ቅድስና ህዝባዊ ዓላማ ለማራመድ የትግል ትልማቸውን ሲቀየሱ ገና ከመጀመርያው በፕሮግራማቸው መግቢያ ላይ “ግዜና ሁኔታን እያየ በሚለዋወጥ ታክቲክ፤ ምንም ግዜና ምንም ሁኔታ በማይለውጠው የሃገር ፍቅር ስቄትና አብዮታዊ ወኔ” ለዚች ሃገር ክብርና ደህንነት ያለማቋረጥ ለመዋደቅ መዘጋጀታቸውን ቃል ገብተዋል። በዚህም ስልት መሰረት በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በሃገር ውስጥ በህቡእ ሲታገሉና ሲያታግሉ ብዙ የመኢሶን አባላት ለእስራት፤ ለቶርቸርና ለስደት ተደርገዋል። በዚህ የማይታጠፍ ቃል መሠረት ደርግ ሥልጣን ላይ ባየባቸው 17 ዓመታት፤ የትግል ስልት በመለዋወጥ መጀመርያ በሙሉ ተቃውሞና በህቡእ፤ ለህዝባችን ትግል ጠቃሚ ሲመስላቸውና እስከመሰላቸው ጊዜ ደግሞ ከ1968 አጋማሽ እስከ ነሐሴ 1969 ዓ.ም. ድረስ ከወታደራዊው መንግሥት ጋር በሂሳዊ ድጋፍ አቋሙ በመሥራት፤ ይህ ታክቲክ ደግሞ ጠቀሜታው ተሟጦ ለህዝባችን ትግል እንቅፋትነቱ ሲያመዝን ከፍተኛ መስዋእትነት የጠየቃቸውን የትግል ስልት ለውጥ በመድረግ ለ13 ዓመታት የደርግን አረመኔ አገዛዝ በህቡእ በመታገል የህዝብ ወገንነታቸውን አስመስክረዋል።

በጊዜው ይህንን ህዝባዊ ፖለቲካችንንና ህልማችንን ወያኔ በትግራይ ክፍለ ሃገር በመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች ላይ ነጭ ሽብር በማስፋፋት ተዋግቶታል። ድርጅታችን በዝያን ጊዜ ለወያኔ ሽብር አልተንበረከከም። የተለምነውና ስፍር ቁጥር ኢትዮጵያውያን የተሰውለት አላማ እንኳን እውን ሊሆን ቀርቶ በሁሉም አንጻር ህዝባችን ተጎናጽፈውት የነበሩት ድሎች እየተቀሙ የባሰ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን ብለን ስለምናምን ለነባሩ ራዕያችን፤ ከህዝባችንና ከሃገራችን ዲሞክራቶች ጎን ቆመን የቆየ ትግላችንን እንገፋበታለን።

ይህንን በግልጽ ካስቀመጥን ዘንድ አሁን ደግሞ የዚህ የፍርድ ቤት ሁለተኛ ገጽታ ወዳልነው በድርጅታችን ላይ ወደሚመሰረተው “የቀይ ሽብር ተዋንያን” ወደሚለው የፈጠራ ክስ እንገባለን። እንዲህ አይኦቱ እስካሁን ድረስ፤ በተራ ወሬና አሉባልታ ሲናፈስ የቆየ ውንጀላ በመሆኑ ወያኔም ሳይቀር ሊጠቀምበት እየሞከረ ነው። በመሆኑም ከተራ አሉባልታ አልፎ መንግይት ነኝ በሚል የፊሲታ ተቆጢታ ወንጀለኛ ቡድን በይፋ በመቅረቡ በዚህ ጉዳይ ያለንን አስተሳሰብና አቋም እንደሚከተለው ባጭር ባጭሩ እናቀርባለን።

1ኛ. ቀይ ሽብር ምንም እንኳን እጅግ የሚዘገንና የግፍና የጅምላ ግድያ ወንጀል ቢሆንም ባለፉት 20 ዓመታት ለብዙ ኢትዮጵያውያን ደምና እንባ መፍሰስ ምክንያት የሆነው አስከፊ የአመጽ ሂደት አንድ ገጽታ ብቻ ነው። ባለፉት 20 ዓመታት ይህ ሰማእት ህዝባችን ከአስከፊው ቀይ ሽብር በተጨማሪ ከነጭ ሽብር አንስቶ በአብዮት ግርግር እስከተፈጸመ ግለሰባዊ የቂም በቀል ግድያዎች፤ በደርግ፤ በወያኔና በሻቢያ ከተፈጸሙ የጦር ሜዳ ወንጀሎች እስከ ቡድኖች የእርስ በርስ ፍጅት፤ ከባአድ ወረራ እስከ ተገንጣዮች አመጽ እየተፈራረቀበት የተንገላታና የደም እንባ ያነባ ህዝብ ነው። ካለፈው እንማር፤ ይህ ዛሬም ያላበራው የግፍ ዘመን ያክትም፤ ተመልሶም አይምጣብን ብለን ከተነሳን ያለን አንድ

መንገድ ብቻ ነው። በግርግር ሳይሆን በጥሞናና ትምህርት በሚሰጥ ሁኔታ ከላይ በዘረዘርናቸው የአመጽ ዓይነቶች ሁሉ በተሳተፈና አሁንም በህዝባችን ላይ ይህ ነው የማይባል ግፍ በመፈጸም ላይ ባለ ቡድን በተቋቋመ ፍርድ ቤት ሳይሆን በነጻና ገለልተኛ አካል፤ በዚህ ግፍ አስከፊ ገጽታ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በህዝባችን ላይ በተፈጸመው አመጽ ላይ አተኩሮ ምርምር ማካሄድና ወንጀለኞችን ሁሉ ለፍርድ ማቅረብ ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ የዚህኛው ኢትዮጵያዊ ንጹህ ደም ከዚያኛው ኢትዮጵያዊ ይበልጣል የማለትን ያህል ይዘገንነናል። ይህ ካልሆነ ድረስ የሚሞከረው ሁሉ በቀይ ሽብር አሰቃቂ ግፍ የፖለቲካ ንግድ ለማካሄድ መሞከር ስለሆነ ከየትኛው ወገን ይሁን ከየትኛው የተሰውትን ዜጎቻችንን እንደገና እንደመግደል፤ ቀሪ ዘመድ አዝማድን እንደገና ለሃዘንና ለሰቆቃ እንደመዳረግ የመሰለ አስጸያፊ ተግባር ነው።

2ኛ. የመላ ኢትዮጵያ ሶሽያሊስት ንቅናቄ በሂሳዊ ድጋፍ አቋሙ በይፋ ከወታደራዊው መንግስት ጋር ሲሠራም ሆነ በህቡእ በተቃዋሚነት ሲታገል በሁለቱም ወቅቶች ስፍር ቁጥር የሌላቸው አባላቱን የሰዋ እንጂ ምንም ጊዜ የጅምላና የግፍ ግድያን ያራመደ ድርጅት አይደለም።

የ1969 ዓ.ም. ሁኔታ እንመልከት። በዚህ ዓመት መኢሶንና ደጋፊዎቹ የበላይነት የያዙባቸው ሁለት ወራት የየካቲትና የመጋቢት ወራት ብቻ ናቸው። እነዚህ ሁለት ወራት ከቀደሟቸው አምስት ወራትና በተለይ ደግሞ ድርጅታችን በነሐሴ 1969 ህቡዕ ከገባ በኋላ በ1970 ዓ.ም. ከተከሰቱት የምጽአት ወራት ጋር ሲነጻጸሩ “ደም የጠማቸው” ወራት ሊባሉ እንደማይችሉ ማንኛውም ሃቀኛ ዜጋ ሊመሰክረው የሚችለው ሃቅ ነው።

በነዚህ ወራት በግድያ ተሳትፈዋል ብቻ ሳይሆን ሊሳተፉ ይችላሉም ተብለው የሚጠረጠሩ ብዙ ሰዎች ታስረዋል። ዋናው ትኩረት ትጥቅ ማስፈታት ላይ ስለነበረም ሁለት አሰሳዎች በስነ ሥርዓት ተካሂደዋል። በዚህን ጊዜ አላስፈላጊ የሆኑ ግድያዎች እንዳይካሄድ ሲል ድርጅታችን ለሚታጠቁ ኃይሎች አንዳንዴ እስከሶስት ሳምንት የሚፈጁ ሴሚናሮች አካሂዷል። የግፍ ግድያ እንዳይኖር በመገናኛ ብዙሃን ሳይቀር ምን ዓይነት መግለጫዎች ይሰጡ እንደነበር ለመረዳት ዛሬ መለስ ብሎ የወቅቱን የመንግሥት ጋዜጣዎች ማገላበጥ ብቻ ይበቃል። የዚህ በሃላፊነት በተመላ ፖሊሲ ውጤት ምን እንደሆነ ግልጽ ነው።

መኢሶን ከደርግ ከተለየ በኋላ በተከተለው የመአት ዘመን ብጣሽ የተቃዋሚ ወረቀት የተገኘበት ወጣት ሆነ ሌላ ዜጋ በዚህ ሰብብ እንደቅጠል ረግፏል። በመኢሶን ሥር በተካሄዱት ሁለት አሰሳዎችና የትጥቅ ማስፈታት ዘመቻዎች በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ከባድና ቀላል መሣሪያዎች ከየግለሰቦች ቤት ተሰብስበዋል። መሣሪያ ተገኘባችሁ ተብለው በዚህ ብቻ፤ እንኳን የተገደሉ የታሰሩ ዜጎች የሉም።

መኢሶን ከደርግ ከተለየ በኋላ በተከተለው የመዓት ዘመን አንድ ሺ ግርማ ከበደዎች በመንግሥት አይዟችሁ ባይነት ዜጎችን በግፍ እየገደሉ፤ አስከሬናቸውን እንደ ውሻ በየመንገዱ እየጣሉ በሃገራችን ታይቶ የማይታወቅ አሰቃቂ ግፍ ፈጽመዋል። መኢሶን የበላይነትን በያዘባቸው የካቲትና መጋቢት 1969 የሰደድ ምልምል ግርማ ከበደ 9 ዜጎችን በግፍ በመግደሉና ሬሳቸውንም መንገድ ላይ በመዘረሩ ከጊዜው መንፈስና ፖሊሲ ተቃራኒ ተግባር በመፈጸሙ ወድያውኑ በሞት ቅጣት ተቀጥቷል።

መኢሶን ከደርግ ተለይቶ ከየአቅጣጫው እየተዋከበ በነበረበት 1970 ዓ.ም. ቢሆን ባለው አቅም ራሱን ለመከላከል እየሞከረ ይካሄድ የነበረውን ቅጥ ያጣ ግድያ ለመቃወም የቻለውን ያህል ታግሏል። በእነዚህ አስከፊ ወራት ነባር መሪዎቹ ከተሰው በኋላ በዚያ ቀውጢ ሰዓት የድርጅቱን አመራር አደራና ሃላፊነት የተረከቡ ጓዶቻችን ከውስጣቸው ብዙዎቹ በውስጥ ከሃዲዎችና በአደር ባይ ድርጅቶች እየተጠቁ ተራ በተራ ከመሰዋታቸው በፊት የእልህና የበቀል ፖለቲካ አልተከተሉም። ያን ጊዜ የተከተሉትና ዛሬ

እጅ የምንኮራበት ፖሊሲያቸው አባላትም ማህበራት በምንም አይነት በቀይ ሽብሩ ዘመቻ እንዳይሳተፍ፤ ተቃዋሚ ናቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ዜጎችን እንዲያስሩና እንዳይጠቁሙ፤ የታሰሩ ዜጎችን በማስሎቹ የቀይ ሽብር አራማጅ ተብሎ የሚወነጀለው ድርጅታችን ይህንን መመርያ በመከተል ከግፍ አንሳተፍም በማለታቸው "በጸረ አብዮተኝነትና" "በቀኝ መንገደኛ ነት" እየተወነጀሉ ብዙ የቀበሌ ተመራጭ አባላት የተሰውበት ድርጅት ነው።

3ኛ. መላ ኢትዮጵያ ሶሽያሊስት ንቅናቄ የቀይ ሽብር ሰለባ ብቻ ሳይሆን የግፍና የግድያ ወንጀሎች በየዓይነቱ የተፈራረቁበት ድርጅት ነው። መኢሶን እንደ ወቅቱና እንደሃገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ፤ አንድ ጊዜ ባንዳ ሌላ ጊዜ ቀኝ መንገደኛ፤ አንዴ የጠላት ሠርጎገብና ጠባብ ብሄርተኛ፤ ሌላ ጊዜ ትምክተኛ፤ ደርግን ሲቃወም ሆነ ከጎኑ ተሰልፎ በጸረ ፊውዳሉ ትግል ሲሳተፍ ለዚህ ትግል ድል ለማጎናጸፍ ከገበሬው ጎን ሆኖ ሲታገል ሆነ እነዚህ ድሎች ተመልሰው እንዳይነጠቁ ከሃገሪቱ ዲሞክራቶች ጎን ተሰልፎ ሲተናነቅ ይህ ነው የማይባል መስዋእትነት የገበሬ ድርጅት ነው። መኢሶን በነጭና በቀይ ሽብር ብቻ ሳይሆን፤ በሰደድና በሌሎች አፍቃሪ ደርግ ድርጅቶች በሚሊተሪውና የፖሊስ ቢሮክራሲ ሥውር ኮማንዶዎች፤ በየክፍለሃገሩ በተሰየሙ የደርግ አባላት መንግሥታዊ ትእዛዝና ውሳኔ በደርዘን ሺ የሚቆጠሩ ታጋዮቹን ሰውቷል። በያለበት የወደቁት የገበሬና የወዛደር ማህበራት መሪዎች፤ የሴቶችና የለጋ ወጣቶች፤ የምሁራንና የዲሞክራቶች፤ የመለዩ ለባሾችና አገር ወዳድ ዜጎች ደምና ጢሪ ያጡ ወላጆችና አሳዳጊ ያጡ ሕጻናት እንባ ቀጭን ውሃ ነው ካልተባለ ስለግፍና አመጽ ሲነሳ መኢሶን በነዚህ ሁሉ ሰማእታት ስም የሚፋረድ እንጂ የሚፈረድበት ድርጅት አይደለም።

4ኛ. ይህ ሁሉ ስለተባለ የመኢሶን ግለሰብ አባላትና ደጋፊዎች ከድርጅቱ ፖሊሲ ውጭ ግፍ አልፈጸሙም ማለት አይደለም። ከነዚህ ግለሰቦች ውጭም ድርጅታችን ህቡዕ እንደገባ ራሳቸውን "የመኢሶን ግራ ክንፍ" ብለው በታሪካችን የሌለ አንጃ ፈጥረው ከደርግ ጋር በደርግ እርዓታ አንድ ሰሞን ውር ውር ያሉ በድርጅታችን ስም ወንጀል የፈጸሙ የሉምም ማለት አይደለም። እነዚህ ጥቂት ግለሰቦች የጥፋት ተግባራቸውን የጀመሩት የመኢሶንን አመራርና ሌሎች አባላት እየጠቆሙ ለደርግና ለሞት በመዳረግ እንደሆነ ስለሚታወቅ ማንም አእምሮ ያለው ሰው በነሱ ወንጀል መኢሶንን ተጠያቂ ማድረግ አይችልም። እነዚህ ከሃዲዎችም ሆኑ የግፍ ተግባር የፈጸሙ የመኢሶን አባላት አንድ ቀን ከፍርድ ፊት መቅረብ ይኖርባቸዋል። ራሱ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው ወያኔ በሰየመው ፍርድ ቤት ሳይሆን ይህንን የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን በጥሞናና ምንም አድልዎ በሌለበት ሁኔታ የሚመረምር አካል ሲኖር እነዚህም ግለሰቦች ለፍርድ መቅረብ ስለሚኖርባዥው ድርጅታችን አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም ትብብር እንደሚያደርግ ከወዲሁ ለማረጋገጥ እንወዳለን።

እንዲህ አይነቱ ገለልተኛ አካል ራቱ በወንጀል ተጠያቂ በሚሆነው በወያኔ መንግሥት ሥርም ሆነ ሌላ እሱን በሚተካ ጸረ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ሊቋቋም የሚችል አካል አይደለም። ይህ አይነቱ ፍትሃዊ አሠራር እንዲመጣ በቅድሚያ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መታገል ስለሚያስፈልግ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ጎን ተሰልፈን ትግላችንን እንቀጠላለን። ይህ ስለተባለ ግን እስከዚያው ድረስ የሰወማእቶቻችን ስም በአሉባልታ ሲጎድፍ፤ አጸፋ ከመስጠት አንመለስም። የወያኔ ፍርድ ቤት ሊያቀርባቸው ለሚሞክራቸው ውንጀላዎች ሁኔታዎችን፣ ወቅቶችንና ሥፍራዎችን በአሃዛዊና በሌሎች መረጃዎች እያስደገፍን መልስ እንሰጣለን።

ዛሬም በድርጅታችን ውስጥ የተካተቱም ሆነ የቀድሞ አባላትና ደጋፊዎቻችን ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን ለእውነት መቆም ለዲሞክራሲ የሚደረገው የጋራ ትግላችን የማይነጠል አካል በመሆኑ በዚህ ሃቁን ለማውጣትና ፍትህን ለመሻት በምናደርገው ጥረት ከድርጅታችን ጋር እንዲተባበሩ ጥሪ እናደርግላቸዋለን።